በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የጉምሩክ ኮሚሽን

THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

CUSTOMS COMMISSION

ቀን ጥር 27 2012

Date

ቁጥር 63/0180/12

Ref.No.

[illegible]

ለሞጆ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ሞጆ

ጉዳዩ፡- በመብራት እቃዎች ላይ የታሪፍ ምደባ አስተያየት መስጠትን ይመለከታል

በቁጥር ሞጉ17.3/17/27 በቀን 07/05/2012 ዓ.ም በተጻፈ ደብዳቤ በአስመጪ Abebe Shifeta ስም በዲ/ዮን ቁጥር 4-28472/19 ተመዝግበው ወደ ሀገር ዉስጥ የገቡ የመብራት እቃዎች ታሪፍ በሽቀጦች የታሪፍ አመዳደብ እቃውን በትክክል ሊገልፀው የሚችል ታሪፍ እንዳላገኛችሁ በመግለፅ በዳይሬክቶሬታችን በኩል ተወስኖ እንዲላክላችሁ መጠየቃችሁ ይታወሳል፡፡

ስለሆነም አስፈላጊውን ማጣራት በማድረግ የተሰጠዉን የታሪፍ አመዳደብ አስተያየት ሁለት ገጽ አባሪ አድርገን የላክንላችሁ መሆኑን እየገለፅን ለቀጣይ ተመሳሳይ ጥያቄ ሲኖራችሁ በታሪፍ አመዳደብ መጠየቂያ ቅፀ መሰረት ጥያቄያችሁን እንዲታቀርቡ እየገለፅን ሌሎች ቅ/ፅ/ቤቶችም በተሰጠው የታሪፍ አመዳደብ አስተያየት መሰረት እንዲያስተናግዱ በግልባጭ እንዲያውቁት ተደርጓል፡፡

ከሰላምታ ጋር

ጌቱ ለገሰ አ/ጫ.

የታሪፍ ምደባና ምረት አገር አመዳደብ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ግልባጭ፤

- ለታሪፍ ምደባ አሰራርና ድጋፍ ቡድን

  ጉምሩክ ኮሚሽን

- የጉምሩክ ሥነ-ሥርአት ለሚፈጸምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

  በያሉበት

ለዘመናዊና ፍትሀዊ የታክስና ቀረጥ አስተዳደር ሥርዓት ግንባታ ተግተን እንሰራለን!!

☎ +251 116 62 98 00
📠 +251 116 62 98 19
✉ 2559
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa,Ethiopia

- ለአዲስ አበባ ቃሊቲ /ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
- ለአዲስ አበባ ኤርፖርት ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  አዲስ አበባ
- ለሞጆ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  ሞጆ
- ለባህርዳር ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  ባህርዳር
- ለኮምቦልቻ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  ኮምቦልቻ
- ለድሬዳዋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  ድሬዳዋ
- ለጋላፊ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  ጋላፊ
- ለጅግጅጋ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  ጅግጅጋ
- ለጅማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  ጅማ
- ለሞያሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  ሞያሌ
- ለመቀሌ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  መቀሌ
- ለአዳማ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  አዳማ
- ለአዋሽ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  አዋሽ
- ለአዋሳ ጉ/ቅ/ጽ/ቤት
  አዋሳ

# በኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን

## የዕቃዎች ታሪፍ አመዳደብ አስተያየት መስጫ ቅጽ

1. የዕቃው ዝርዝር መግለጫ

1.1 **የዕቃው ስም**፡- wall light, down light, spot light, flood light, panel light

1.2 **የዕቃው ምንነት**፡- ቅ/ፅ/ቤቱ ከላከው ሰነድ እና በስልክ ካደረግነው ውይይት ለመረዳት እንደተሞከረው እቃዎቹ የተለያዩ አይነት መብራቶች መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

1.3 **የሚሰጠው አገልግሎት**፡- ይህ ጥያቄ የቀረበባቸው የመብራት እቃዎች ቅ/ፅ/ቤቱ ከላከው መረጃ ለመገንዘብ እንደተቻለው በተለያየ ቦታ ላይ በማስቀመጥ ብርሃን ለመስጠት የሚያገለግሉ መሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

2. ጥያቄዉን ያቀረበዉ ቅ/ጽ/ቤት ወይም ሌላ አካል ዕቃውን የመደበበት የታሪፍ ቁጥር

9405.10/9405.40

3. የታሪፍ ምደባና ስሪት አገር አወሳሰን ዳይሬክቶሬት ዕቃውን የመደበበት የታሪፍ ቁጥር

9405.1000/9405.2010/9405.2020/9405.4010/9405.4020

4. የታሪፍ ምደባ አስተያየቱ የተሰጠበት ምክንያት (የታሪፍ አመዳደቡ ዝርዝር መግለጫ)

ከላይ በተጠቀሰው የእቃው መግለጫ እና አገልግሎት አንፃር የእቃዉን ታሪፍ ኮድ ለመመደብ በአንቀጽ 94.05 ስስት የታሪፍ ንኡስ አንቀጾችን ማየት ያስፈልጋል:-

9405.10 ባለ ዘርፍ ተንጠልጣይ የጣራ መብራቶች እና ሌሎች የጣራ ወይም የግድግዳ የኤሌክትሪክ መብራቶች መገጣጠሚያዎች (Chandeliers and other electric ceiling or wall lighting fittings)፣የውጭ ህዝባዊ አደባባዮችን ወይም የማለፊያ አውራ ጎዳናዎችን ለማብራት የሚያገለግሉትን አይነቶች ሳይጨምር የሚመደቡበት የታሪፍ አንቀፅ ሲሆን በዚህ የታሪፍ ንኡስ አንቀፅ ላይ ሊመደቡ የሚችሉ እቃዎች በኤሌክትሪክ የሚሰሩ ሁነው ባለ ዘርፍ ተንጠልጣይ የጣራ እና ሌሎች የጣራ ወይም የግድግዳ መብራቶች ብቻ ሲሆኑ፤ ይህም ማለት በዚህ የታሪፍ ንኡስ አንቀጽ የሚመደቡ እቃዎች የፀሃይ ሃይል የሚጠቀሙ ቢሆኑም ባይሆኑም፣ በLED/CFL እንዲሰሩ ዲዛይን የተደረጉ ቢሆኑም ባይሆኑም ከላይ የተገለፁት አይነት እቃዎች ከሆኑ በታሪፍ ቁጥር 9405.1000 ላይ የሚመደቡ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

9405.20 የጠረንጴዛ፣ የዴስክ፣ የአልጋ ኮመድኖ ወይም በወለል ላይ የሚቆሙ የኤሌክትሪክ መብራቶች የሚመደቡበት የታሪፍ ንኡስ አንቀጽ ነው። ይህም ማለት በዚህ የታሪፍ ንዑስ አንቀፅ የሚመደቡት መብራቶች ጣራ ላይ ወይም ግድግዳ ላይ በመሆን መብራት የሚሰጡ ሳይሆን ጠረንጴዛ ላይ፣ ዴስክ ላይ፣ የአልጋ ኮመድኖ ላይ ወይም በወለል ላይ በመቆም አገልግሎት የሚሰጡ ተንቀሳቃሽ መብራቶች ሲሆኑ የፀሃይ ሃይል እንዲጠቀሙ ዲዛይን የተደረጉ እና በLED/CFL እንድሰሩ ዲዛይን የተደረጉ ከሆኑ በታሪፍ ቁጥር 9405.2010 ላይ የሚመደቡ ሲሆን የፀሃይ ሃይል የማይጠቀሙ ሆነው ነገር ግን በLED/CFL እንድሰሩ ዲዛይን የተደረጉ ከሆኑ በታሪፍ ቁጥር 9405.2020 ላይ የሚመደቡ ይሆናል።

9405.40- ሌሎች የኤሌክትሪክ መብራቶችና የመብራት መገጣጠሚያዎች ማለትም ከላይ ከተጠቀሱት የታሪፍ ንዑስ አንቀፆች (9405.10 እና 9405.20) እንዲሁም ለገና ዛፍ ማስጌጫ (9405.30) አይነት ከሚሆኑት መብራቶች ውጪ ያሉ የኤሌክትሪክ መብራቶችና የመብራት መገጣጠሚያዎች የሚመደቡበት የታሪፍ ንዑስ አንቀፅ ሲሆን፤ በዚህ የታሪፍ ንዑስ አንቀፅ የሚመደቡት መብራቶች የፀሃይ ሃይል እንዲጠቀሙ ዲዛይን የተደረጉ እና በLED/CFL እንድሰሩ ዲዛይን የተደረጉ ከሆኑ በታሪፍ ቁጥር 9405.4010 ላይ የሚመደቡ ሲሆን የፀሃይ ሃይል የማይጠቀሙ ሆነው ነገር ግን በLED/CFL እንድሰሩ ዲዛይን የተደረጉ ከሆኑ ደግሞ በታሪፍ ቁጥር 9405.4020 ላይ የሚመደቡ መሆኑን እየገለፅን የእቃዎቹን ሁኔታ እና የሚገጠሙበትን አግባብ በቅ/ጽ/ቤታችሁ በኩል በማጣራት ከላይ በተገለፀው ማብራሪያ መሰረት በመመደብ ማስተናገድ የምትችሉ መሆኑን ለማስገንዘብ እንወዳለን።

5. ለታሪፍ አመዳደብ አስተያየቱ የተጠቀሱ ዓለም ዓቀፍ የታሪፍ አመዳደብ ህጎች (Classification Rules)

ደንብ ቁጥር 1፣ እና 6

አስተያየቱን ያዘጋጀው የታሪፍ ምደባ ባለሙያ ስምና ፊርማ
ስም-የኑስ ጠቢያው
ፊርማ-

አስተያየቱን ያረጋገጠው የታሪፍ ምደባ ቡድን መሪ ስምና ፊርማ
ስም- እንዳለ ይመር
ፊርማ-

Ethiopian Customs Commission